**<u>ደቻቱ</u>**

ዘንድሮስ አቈመ ደቻቱ
አለወርድ አለስፋቱ
ተንጠራራ አለቁመቱ
አለ ግዜው አለሰዓቱ

ሊስተካከል ከሰቲት፡ከመረብ ካዋሽ ከገናሌ
ከጥቁር ዐባይ፡ ከኦሞ ወንዝ ከሸበሌ
ከበሽሎ፡ ከሙገር፡ ከዴዴሳና ከግቤ
ከአኮቦ፡ ከባሮ፡ ከዠማና ከተከዜ

ከዓመት ዓመት ምሱ እንዳይቀር
ከጭቃ ሹም ከምስለኔው ሊተባበር
ሊከፍል የአድባር፡ የቀሌ ዕዳ
ሊሰዋ የሰው የእንሰሳ ጭዳ

ደቻቱ ዘንድሮስ ገነነ
ካጥፊዎች ጋር ወገነ
በለፍቶ አዳሪው አልታመነ
ባዘንተኛው በያለበት ተኮነነ።

እንደዱር አውሬ፡ እንደዳቢሎስ ጨለማን ተገን አርጎ
ከድሬ አፋፍ ከደንገጎ፡ ከጋራው ጫፍ ተመስጎ
ደመናውን ከሰማይ ጎትቶ ሰቦ፡ በአሸዋ ውስጥ አስርጎ
አሰሱንም ገሰሱንም ንፍሳቱንም አጨናንቆ፡ ባንድ አድርጎ
እንስሳውን ግውዙን የቤት ዕቃና ፍራሹን አደባልቆ
ላይመልስ ወሰዳቸው መቶዎቹን ባፍታ ጠርጎ።

ዕድሜ ጾታ ሳይለይ፡ በጨለማ አሽምቆ፡ አሰልቶ
ግዳዩን በየፈፋው በየሜዳው አስመስክሮ፡ የሬሳ ስጥ አሳይቶ
የሌሎቹን በሆዱ ቀብሮ፡ በክምር አሸዋ ደብቆ
ካደጉበት ከቀያቸው ከሰው መኖሪያ ወዲያ አርቆ
ፊቱ ያገኘውን ሁሉ ጠራርጎ ገፍቶ አንሳፎ
ለቋሚ ዘመድ፡ ለቀባሪ እርም ነፍጎ

ዶሮ ሰይጮህ ፀጥ አረገው
ከህልም ተሰፋው ሳይነቃ
ጠግቦ በልቶ ሳይጠረቃ
እንደተኛ በዚያ አስቀረው
ረጅም ዕቅዱን ባጭር ቀጨው።

እኮ ምን አለ አፈቴሳ፡ ማሪያም ሰፈር፡ ኮካኮላ?
መናኸሪያ፡ ጫት ማህበር፡ ያቀፊራ
ገንደ ምስኪን፡ አዲስ ከተማ
መስጂድ፡ ጥምቀተ ባሕር፡ ያመጋላ

እኮ ምን አለ፡ ኛንጋቶም፡ ምንስ አለ ግሪክ ካምፕ?
ምን ተናገረ ዳሰነች፡ ምን መከረ ነምበርዋን?
ገንደ ቆሬ፡ አሞራቴ፡ ሳቢያን ድልድይ
ሸልሌ፡ ያደወሌ፡ ኮኔል መንደር?

ምን አፍ አለው ምንስ ይበል?
ደቻቱ በድንገት ሳይታሰብ ሲገነፍል
የድሬን ሕዝብ ከፍልስጥኤም፡ ከሊባኖስ ሊያመሳስል
ከኢራቅ የሕዝብ ፍጅት፡ ሊፎካከር ግዳይ ሲጥል።

ምንስ ይበል ትንፋሽ ገመዱ በቅጽበት ሲበጠስ?
ደቻቱ ጎርፍ ውሃውን፡ እንዳዳፍኔ፡ እንደመድፉ ሲተኩስ

ከቦምብ ናዳ ከመትረየስ ከታንክ ድርምስ
አንድ ሆኖበት
ሰውም ሰውን፡ ተፈጥሮውም ሰውን ሲጨርስ።
ሳንባ በሽታ ወባና ኤድሱ ጊዜ ሲሰጡ
ድሬዎች ከላኤ ጎርፍ ሳይሰሩ፡ ወይ ሳያሰሩ
ወይ ወደ ሌላ ቀዬ ሳይሰፍሩ፡ ወይ ሳይዘምቱ
በድንገቴው ፈጥኖ ደራሽ በአግአዚው በደቻቱ
ባንድ ሌት ጎርፍ ሳያስቡት ተመቱ።
እንደተኙ ሳይነቁ፡ በጎርፍ መርከብ ተንሳፈፉ
ሕፃን፡ ሴት፡ አዛውንት ባንድ ቀን ደፍ ተቀጠፉ
አለግብር ሃጢያታቸው በደራሽ ውሃ ተቀጸፉ
ቤተሰቦች፡ መንደሮች፡ ባንድነት ተጠነፈፉ
ዓላማ ግባቸው ከነሱው ጋር፡ ተጠቃለው ረግፉ።
ግዳይ ጣለ ደቻቱ፡ ጨኾ፡ ፎከረ፡ አቅራራ
ከደንገጎ እስከ ከዚራ
ባለሳምንቱን ባለተራ
ከአዋሽ፡ ከሸበሌ፡ ከኦሞ ጋር ተጠራራ።
ከሱናሚው ሊወዳደር፡ እኩል ሊሆን ከሀሪከን
ሊያከብርልን መብታችንን
የዕልቂት፡ የፍጅት፡ የሞት “ቡፌ” ሊያማርጠን
ጉሮ ወሸባ ዘፈነብን።
መንግስት ሊያለማን ብሎ ሊያዘምነን
መናኸሪያ ሊያበጅልን
ልክ እንደ ራጉኤል እንደ ቂርቆስ
“ለኛ ብሎ” “ታይዋን” ገበያችንን ቢያነድብን
ፌዴራሉ፡ ፈጥኖ ደራሹ፡ ከተፎው
አግአዚው ደቻቱ፡ አሸምቆ ደረሰልን
ከካድሬ ጩኸት ከግብር ዕዳ ገላግለን።
ሳንነቃ ጠራረገን፡ ላይመልሰን ወሰደን
ከኑሮ ጣጣ ፈንጣጣ ነፃ ሊያወጣን
የሞት ድልድይ አሻገረን።
ልክ እንደ ዐባይ፡ አፈር አሸዋ አስጨብጠን
እንደ አግአዚ ወዳልታወቀው አጋዘን።
አደሬ እንሁን ሱማሌ፡
አማራ ወይ ጉራጌ
ኦሮሞ ሲዳማ ወላይታ
ወይ ትግሬ ወይ ከምባታ
ዘራችንን ሳይጠይቀን
አንዳችንን ባንዳችን ላይ ደበላልቆ ረመረመን
ሸበሌ ላይ፡ ኦሞ ላይ፡ አዋሽ ላይ ወስዶ ከተመን
ደቻቱ ጨረሰን፡ በየሰርጡ ፈገመን
ድሬ ሜዳ አንድ አድርጎ ፈጸመን።

ታፈሰ ውብሸት
ሎስ አንጀለስ 8/17/06

*(በነሐሴ ወር 1998 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ወንዞች የክረምት ጎርፍ ሙላት በድሬደዋ፡ በአዋሽና በኦሞ ወንዝ አካባቢ ሕይወታቸውን፡ ንብረታቸውን፡ ቤተሰቦቻቸውንና ከብቶቻቸውን በድንገት ላጡትና ከቀያቸው ለተፈናቀሉ ዜጎች መታሰቢያ ይሁን)*